# ገብር ኄር

## ታማኝ አገልጋይ

ዐቢይ ጾም ወይም ሁዳዴ ጌታ ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ወደ ቆሮንቶስ ተራራ ሄዶ፣ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት የጾመው ጾም ነው። ዐቢይ ጾም ስምንት ሳምንታት ሲኖሩት እያንዳንዳቸውም የራሳቸው መጠሪያ አላቸው። ይህም መጠሪያቸው፣ ዘወረደ፣ ቅድስት፣ ምኵራብ፣ መጻጉዕ፣ ደብረ ዘይት፣ ገብር ኄር፣ ኒቆዲሞስ፣ ሆሣዕና ይባላሉ።

ከዚህ ቀጥሎ ስድስተኛውን ሳምንት ገብር ኄር – ታማኝ አገልጋይ ተብሎ የሚጠራውን እንመለከታለን። ገብር ኄር የተባለውም ጌታው በእምነት የሰጠውን መክሊት አትርፎ ስለ መለሰው አገልጋይ ምሳሌ የሚነገርበትና የሚነሣበት ስለ ሆነ ነው (ማቴ.፳፭፥፲፬–፴)።

ጌታችን እንዳስተማረውና ቅዱስ ማቴዎስ እንደ ጻፈው፣ አንድ አገልጋይ ከጌታው የተቀበለውን መክሊት አትርፎበት ዕጥፍ አድርጎ በመመለሱ፣ «አ ገብር ኄር ወምእመን፣ አንተ የታመንክ ቸር አገልጋይ» ብሎ ጌታው ስላመሰገነው፣ በዚህ ምክንያት በአገልጋዩ ስም ዕለቱ «ገብር ኄር» ተብሎ ይጠራል (ማቴ.፳፭፥፲፬–፴፩)።

እምነትን ከተትረፈረፈ መልካም ሥራ ጋር አስተባብሮ ይዞ የተገኘ ሰው፣ በጌታ ዘንድ ታማኝ አገልጋይ ተብሎ በመንግሥተ ሰማይ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያገኝ ጌታችን በምሳሌ ያስተማረውን እንመልከት:-

«እስመ ከመ ብእሲ ዘይነግድ ወጸውዐ አግብርቲሁ ወወሀቦሙ ንዋዮ ይትገበሩ ቦቱ፤ ወደ ሌላ ሀገር የሚሄድ ሰው፣ አገልጋዮቹን ጠርቶ ይሠሩበት ዘንድ መክሊቱን ሰጣቸው። እንዲህም ሆነ:- ለእያንዳንዱ እንደ ዐቅሙ ለአንዱ አምስት መክሊት፣ ለሁለተኛው ሁለት መክሊት፣ ለሦስተኛው አንድ መክሊት ሰጣቸውና ወዲያውኑ ወደ ሌላ ሀገር ሄደ።

አምስት መክሊት የተቀበለው ሰው ሄዶ ነገደበት፤ ሌላም አምስት መክሊት አተረፈ። እንዲሁም ሁለት መክሊት የተቀበለው ነገደበትና ሌላ ሁለት መክሊት አተረፈ። አንድ መክሊት የተቀበለው ሰው ግን ሄዶ ምድሪቱን ቆፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ።

ከብዙ ዘመን በኋላ የእነዚያ አገልጋዮች ጌታ መጣና ሲቆጣ ጠራቸው፣ አምስት መክሊት የተቀበለው ሰው ወደ ጌታው ቀረበና ያተረፈውን ሌላ አምስት መክሊት ጨምሮ ሲያስረክብ፣ «ጌታ ሆይ፣ አምስት መክሊት ሰጠኸኝ፤ እነሆ አምስት መክሊት አተረፍኩበት» ብሎ ሰጠው።

ጌታውም፣ «መልካም፤ አንተ በጎ ታማኝ አገለጋይ በጥቂት ታምነሃል፤ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» አለው።

ሁለት መክሊት የተቀበለው ደግሞ በተራው ቀርቦ፣ ‹ጌታ ሆይ፣ እነሆ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፣ እነሆ ሁለት መክሊት አተረፍኩበት› አለና አስረከበ።

